# ይህ የሚሆን ከሆነ እቤት ያቆዩኝ ...

**100.4°F (38°C) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሰውነት ሙቀት መጠን አለኝ**



- እድሜዬ ከ 2 ወር በታች ነው; ወይም
- እድሜዬ ከ2 ወር በላይ ሆኖ **ሌሎች የሕመም ምልክቶች አሉኝ** (የጉሮሮ ህመም፣ የጆሮ ህመም፣ ራስ ምታት፣ ሽፍታ፣ ማስታወክ፣ ተቅማጥ) ወይም **ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ አይደለም**

**እያስመለሰኝ ከሆነ**



በ 24 ሰዓታት ውስጥ 2 ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ካስመለሰኝ

**ተቅማጥ ከያዘኝ**



- በ 24 ሰአታት ውስጥ ለልጅ ልምድ ከሆነው በላይ ማለትም ከ2 ጊዜ በላይ ለየት ያለ ውሃማ የሆነ ሰገራ ካለኝ፣ ወይም
- በሰገራ ውስጥ ማንኛውም ደም ወይም የተዝለገለገ ንፍጥ የሚመስል ፈሳሽ ካለኝ

**ሽፍታ፣ ቁስሎች፣ ቅማል፣ ጭርት ወይም በቆዳ ላይ የሚወጣ ፈንገስ ካለኝ፣ ወይም እያሳከከኝ ከሆነ**



- የሰውነት ሽፍታ (ከአለርጂ ፣ ዳይፐር ወይም ሙቀት ጋር የተያያዘ ውጤት ካልሆነ)
- መግል ያላቸው ክፍት ቁስሎች
- ከለሃጭ መዝረክረክ ጋር የተያያዙ የአፍ ቁስሎች
- ያልታከመ የጭንቅላት ቅማል፣ ጭርት ወይም እከክ

**ብቻ በጣም ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ አይደለም**



- ያልተለመደ ድካም እየተሰማኝ ነው
- የእንቅስቃሴ ደረጃዬ ዝቅተኛ ነው
- የምግብ ፍላጎት የለኝም
- እየተነጫነጭኩ ነው
- ከተለመደው በላይ እያለቀስኩ ነው
- የፕሮግራሙ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ አልቻልኩም

እባክዎን ያስተውሉ፡ ከ 2022 ጀምሮ፣ የአሜሪካ የሕፃናት ሕክምና አካዳሚ 100.4°F (38°C) ወይም ከዚያ በላይ የሆነን የሰውነት የሙቀት መጠን ትኩሳት እንደሆነ ይገልጻል።

**በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ህመም COVID-19 ብቻ አይደለም።** የሕጻናት እንክብካቤ መስጫ ማእከሎች እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞች የ Washington Administrative Code [WAC] 110-300-0205 በመከተል ልጆች እና ሰራተኞች በሚታመሙበት ጊዜ ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ማድረግ አለባቸው።

ፕሮግራሞች ከ WAC መስፈርት የበለጠ ጥንቃቄ ያላቸውን የራሳቸውን የበሽታ ፖሊሲዎች ለመጠቀም መምረጥ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ፕሮግራም ህጻናት ወደ እንክብካቤ ከመመለሳቸው በፊት ለ24 ሰአታት ከበሽታው ምልክት ነጻ እንዲሆኑ ሊጠይቅ ይችላል፣ ወይም የ COVID-19 ምልክቶች ያላቸውን ልጆች ከሌሎች አግልሎ ለማቆየት መምረጥ እና አንድ ልጅ ወደ ተቋማቱ ከመመለሱ በፊት አሉታዊ ምርመራ እንዲያሳይ መጠየቅ ይችላል። **እባክዎ የልጆትን የእንክብካቤ ፕሮግራም የበሽታ ፖሊሲ ይከተሉ።**

**ማንም ሰው መታመም አይወድም።** ልጅዎ ሲታመም ቤት ማቆየት መምህራንን፣ ልጆችን እና ሌሎች ቤተሰቦችን ጀርሞች እንዳይዙአቸው ይረዳል። ጤናማ ለመሆን ሌሎች ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች:

- አጅን መታጠብ
- ወቅታዊ የሆኑ ክትባቶችን፣ የCOVID-19ን እና የጉንፋን ክትባቶችንም ጨምሮ በወቅቱ ይውሰዱ
- በተጨናነቀ የህዝብ ቦታዎች ውስጥ በሚያሳልፉ ከሆነ የአፍና የአፍንጫን ጭምብል ማድረግን ከግምት ውስጥ ያስገቡ

ድጋፍ የተደረገው:
Public Health Seattle & King County
SNOHOMISH COUNTY HEALTH DEPARTMENT
2/2023